ጥቅምት 2000 አንዳርጋቸው ጽጌ

## <u>አለባብሰው ካረሱ፣ አይቀር አረም ማፈሱ!</u>

ባለንበት ወቅት ቅንጅት ቀውስ ውስጥ እንዳለ ሁላችንም የምንስማማበት ነው፡፡ በድፍኑ የሚሰነዘሩ አስተያየቶች፣ ክሶችና የተቃውሞ ክሶች፣ ወሬዎችና አሉባልታዎች ችግር አባባሾች እንጂ መፍትሄ መሆን አይችሉም፡፡ ከችግር እንውጣ ከተባለ የሁኔታዎች ጥናትና ግምገማ በእዚህ ላይ የተመሰረተ የችግሮች መፍትሄ መጠቆም መቻል አለብን፡፡ ይህ ደግሞ ከምሁራዊ ስንፍና መላቀቅን፣ በጥድፊያ ጥናትና ምርምር ማድረግን ወደ እቅድ መቀየርን ወደ ተግባር መሸጋገርን ይጠይቃል፡፡ በበኩሌ ቅንጅት እጅግ በጣም ከፍተኛ ችግር ውስጥ ያለ ድርጅት ነው፡፡ ሰሞኑን የሚታየው በአመራሩ መካከል የተከሰተው መከፋፈል የትልቁ ችግር አንዱ አካል ነው፡፡ በኔ እምነት ግን ዋንኛውና ትልቁ ችግር አይደለም፡፡

በሌላ በኩል፣ አሁንም በእኔ እምነት፣ የከፋው ችግር ያለው በወያኔ አማካይነት በቅንጅት ላይ የተፈጸመውና የሚፈጸመው ችግር ነው፡፡ በቅንጅት ውስጥ የተነሳውን ክፍፍል በልመና፣ በሽማግልና፣ በእርቅና በሌላም መንገድ፣ <u>*ነገር ግን ህዝብንና ሃገርን በሚያስቀድም ስሜት በመተራረም፣ የቅንጅት መመሪያ ነው ብለን ለኢትዮጵያ ህዝብ በገለጽነው የዴሞክራሲ መርህ ላይ ተንተርሰን ለመፍታት ብንችልም እንኳን*</u>፣ በወያኔ በኩል ቅንጅትን የመሰለ በህዝብ ተቀባይነትን ያገኘና ህዝብ ተስፋ የጣለበትን ድርጅት እንቅስቃሴ ለማሰናከል የተዘረጋውን ወጥመድ በጣጥሶ ለማለፍ የሚጠይቀው ጥረት፣ ጥብብ፣ ጽናትና መስዋእትንት ቀላል አይሆንም፡፡ ይህንን አደጋና ችግር በሚገባ ዘርዝሮ ማሳየት የሚችል ጥናት ቅንጅትን ከመሰለ የፖለቲካ ድርጅት የሚጠበቅ ነው፡፡ ባለንበት ወቅት ቅንጅት የውስጥ ችግሮቹን ፈትቶ ያለንበትን ፈተኝ ሁኔታ ገምግሞ መላው ትኩረቱ በወያኔ አምባገነናዊ አገዛዝ ላይ ያነጣጠረ መሆን አለመቻሉ መዘዙ አስፈሪ ነው፡፡

ከምርጫ በፊት፣ ከምርጫ በኋላ፣ ከግድያና ከእስር በፊትና ከእስራት በኋላ በሃገሪቱ የፖለቲካ መድረክ የታየውን ሁኔታ በደንብ ማጥናት ሳይቻል ወደፊት ቅንጅት እንዴት ይቀጥል የሚለውን ጉዳይ በአግባቡ ጠይቆ አግባብነት ያለው መልስ መስጠት አይቻልም፡፡ ይህ ተደርጎ ቢሆን በቅንጅት ውስጥ መከፋፋል ቀርቶ ከቅንጅት ውጭ የሚገኙትን የተለያዩ ተቃዋሚ የፖለቲካ ሃይሎችና ሌሎችንም በሃገሪቱ እውነተኛ ዴሞክራሲ ቢሰፍን ተጠቃሚ የሚሆኑትን ትንንሽና ትልልቅ የሲቪክ ማህበራትና ሌሎችንም ድርጅቶች ያካተተ ሰፊ ጸረ ወያኔ የአንድነት፣ የነጻነት፣ የዴሞክራሲና

የእኩልነት ግንባር አስፈላጊነትን መረዳት፣ ይህም እንዲሳካ በጥድፊያና ሳይታክቱ መስራትን የግድ ይል ነበር።

በቅንጅት በኩል ወቅታዊ ሁኔታውን መገምገም ብቻ ሳይሆን ድርጅቱ ሊያነሳቸውና መልስ ሊሰጥባቸው የሚገቡ በርካታ ጥያቄዎች አሉ። ኢትዮጵያን በመሰለ፣ ዘውገ ብዙ፣ ሃይማኖተ ብዙ፣ የጥቅሞችና የፍላጎቶች ስብጥር በሚታይበት ሃገር ወስጥ የተለያዩ ወገኖች በጋራ የተስማሙባቸው ሁሉንም በእኩልነት የሚያስተናግዱ የዴሞክራሲ ተቋማት እንዴት መፍጠር ይቻላል? ነጻ ፍርድ ቤት፣ ነጻ ሚድያ፣ ነጻ የምርጫ ቦርድ፣ ከፓርቲዎች ቁጥጥር ነጻ የሆነ የመከላከያ፣ የደህንነትና የፖሊስ ሃይል ከላይ የጠቀስኳቸውን የተለያዩ ወገኖች በጋራ ባስማማ መልኩ እንዴት ማቋቋም ይቻላል? ቅንጅት ፓርላማ ለመግባት ያስቀመጣቸውን ቅድመ ሁኔታዎች አሁንም እንደሚሰሩ ተናግሯል። በሌላ በኩል ፓርላማ መግባት የሚባል ነገር እንደማይኖር የወያኔ መሪ መለስ ዜናዊ ተናግሯል። ይህ ከሆነ እንዚህ ቅድመ ሁኔታዎች ከምን ጋር ይተሳሰራሉ? በሚቀጥለው ምርጫ ለመሳተፍ? ወይንስ በህገ መንግስቱ የተደነገጉትን ህጋዊ መብቶች በመጠቀም እነዚህን ቅድመ ሁኔታዎች በስልጣን ላይ ያለው መንግስት እንዲቀበላቸው ማታገያ? ወያኔ በህገ-መንግስቱ የተቀመጡትን የመሰብሰብ ሰላማዊ ሰልፍና ሰላማዊ ተቃውሞ የማድረግ መብት በከለከለበት ሃገር ቅንጅት ይሁን ሌላ ተቃዋሚ በገጠርና በከተማ ጽ/ቤቶች ከፈተ አልከፈተ ፋይዳው ምንድነው? እውን ወያኔ በተለይ በምርጫ 97 ያየውን ከስልጣን የመባረር አደጋ ከተረዳ በኋላ ለሌላ ዴሞክራሲያዊ ፉክክር ፈቃደኛ ይሆናል ወይ? ፈቃደኛ ካልሆነ ለማስገደድ ምን ማድርግ ይቻላል? ወያኔ በሚዘውረው የምርጫ ቦርድ አማካይነት ህገወጥ በሆነ መንገድ የቅንጅትን ስም ከፖለቲካ መድረክ ለማጥፋት ወይም ቅንጀት የሚለው ስም ለማይገባቸው አካለት ለመስጠት ቆርጦ ተነስቷል። ይህ ድርጊቱ ምንን ይጠቁማል?

ወያኔ ቅንጅት የሚለውን በሃገራችን የፖለቲካ መድረክ የተናኘውን ስም፣ ሁላችንም ከምናውቃቸው የቅንጅት መሪዎች ለመቀማት በምርጫ ቦርድ በኩል ያሴረው ቅንጅትን በሌላ ድርጅት ስም እንዲደራጅ ለማስገደድ ወይም ወደ ቀድሞ ድርጅቶቹ እንዲበትን ለመግፋት ነው። ይህንን የሚያደርገው ለራሱ ጥቅም ሲል ነው። ቅንጅት በፖለቲካው ገበያ የታወቀ የፖለቲካ ድርጅት ስም ነው። ይህንን እያወቁ ብዙዎች የሞቱለትንና የተሰውለትን ድርጅትና ስም፣ በህዝብ አይምሮ ውስጥ እንዲተከል ብዙ ጥረት የተደረገበትን ድርጅት ወያኔ ስለገፋን ብቻ እንዲያው እንደልባሌ ነገር አስረክበነው ዘወር እንላለን ወይ? ቅንጀት የሚባለውን ድርጅት ለማጥፋት ታጥቆ የተነሳ መንግስት የቅንጅት የቀድሞ ድርጅቶች በተናጠልም ይሁን በጋራ ሌላ ስም ይዘው ቢነሱ የፖለቲካ

እንቅስቃሴ ማድረግ የሚችሉብን ዴሞክራሲያዊ ክፍተት ይለቅላቸዋል ወይ? ወያኔ በመላው ሃገሪቱ በገጠርና በከተማው ህዝብ ላይ ያካሄደው አሰቃቂ ጭፍጨፋ ግምት ውስጥ በማስገባት በርካታ የቅንጅትን አባላትና ደጋፊዎች ማስበርገግ ችሏል:: እነዚህ አባላት የሚረጋጋያና የደህንነታቸው ዋስትን ሳያገኙ ከምርጫ 97 በፊት ሲያደርጉት እንደነበረው በአደባባይ ቅንጀትን ደግፈው የፓርቲውን ደብተር ተሸክመው የገንዘብ እርዳታ ለድርጅቱ ለማድረግ ፈቃደኛ ሆነው በብዛት ይመጣሉ ወይ? ማረጋጊያና የደህንነት ዋስትናስ ቅንጅት ቀሮስቀመጣቸው የዴሞክራሲያዊ ተቋማት ምስረታ ቅድመ-ሁኔታዎች ውጭ ምን ይሆናል? ፈረንጆቹ ዋስትና እንደማይሆኑ ታይቷል:: ያለምንም የደህንነት ዋስትና አባላት እሺ ብለው ቢመጡስ ዴሞክራሲን የተቃዋሚውን ጎራ ለመለየት በተራ የስለላ መሳሪያነት የሚጠቀም መንግስት ባላበት ሃገር፣ አባላትን ለእስራት ለግድያና ለመፈናቀል የሚዳርግን አዲስ ሁኔታ እንዴት ማስቀረት እንችላለን? ቅድሚያ የሚሰጠው ስራ ምን መሆን አለበት? ስማቸውን የማላስታውሰው የአሜሪካ ኮንግሬስ አባል የሆኑ አንዲት ባለቴት HR 2003 በሚመለከተው ስብሰባ ላይ ተገኝተው ትግላችሁን እንድንደግፍ የምትጓዙበትን አቅጣጫ (Road Map) ጠቁሙን ብለው ነበር:: ቅንጅት ከማኒፌስቶው ውጭ አሁን ካለንበት አጣብቂኝ ለመውጣትና አስቀደሞ ድርጅቱ ወዳለመበት ግብ የሚያደርሰንን የትግል ታክቲክና ስትራተጂ ቀይሷል ወይ? የሚያሳዝነው ድርጅቱ በደንብ መንቀሳቀስ ባለመቻሉ ከእዚህ በላይ ባነሳናቸው በርካታ ጉዳዮችና በሌሎችም ላይ ማተኮር አልቻለም:: ይህም በመሪነት ሳይሆን በሁኔታዎች ተጎታችነት ደረጃ የሚያወርደው ይሆናል:: በፖለቲካ 24 ሰአት ረጅም ነው ይባላል:: ደግሞ ደጋግሞ በሃገራችን ታሪክ እንደታየው የፖለቲካ ድረጅቶች በቂ ዝግጅት ሳያደርጉ ሁሉ ነገር መናጋት ሊጀምር ይችላል:: ይህ ሊሆን እንደሚችል ጠቋሚ ነገሮች አሉ:: እንደተለመደው በህዝብ ጫንቃ ላይ የሚሰፍረው ካለፉት ገዥዎች የባሰ ጭራቅ ሊሆን ይችላል::

ይህ በትንንሽ እሳቶች ማጥፋት ስራ ተጠምዶ መሰረታዊ ስራዎችን አለመስራት ከምርጫው በፊት በድርጅቱ ውስጥ ሲታይ የነበረ ነው:: ከምርጫው በኋላ በነበሩት የወከባ ወራትም የጎላ ነበር:: የድርጅቱ መሪዎች እስር ቤት ከገቡ በኋላም የታየ ነው::

ከእስር ከተረፉት የድርጅቱ መሪዎች መሃል መሰረታዊ ጉዳዮች ላይ የማተኮሩን ሃላፊነት በቡድንም ይሁን በግሉም የተረከበ ማግኘት አልተቻለም:: እንዲህ አይነቱን ድርጅታዊ ጉድለት ለማሟለት በማሰብ የተቋቋመው የቅንጅት አለም አቅፍ አመራርም ቢሆን ከአመሰራረቱና በውስጥ ካካተታቸው አስቸጋሪ ባህርይ የአቅምና የብቃት አነስተኛነት በተጠናወታቸው የተወሰኑ ግለሰቦች አማካይነትና የሚጫርን እሳት በማጥፋት ስራ

እንዲጠመድ በመደረጉ ይህንን የጥናትና ምርምር ጉድለት መሸፍን የሚችል እቅድ ማውጣትና ማስፈጸም አልቻለም:: የቅንጅት መሪዎች ከእስር ከተፈቱም በኋላ አሁንም እንደቀጠለ ነው:: ይባሱን ብሎ አሁን ቅንጅት ለማጥፋት እየጣረ ያለው እሳት እንደቀድሞው ከውጭ የሚጫርበት ሳይሆን ከውስጥ ሆኗል:: ይህን ለማጥፋት የሚጠፋው ውድ ግዜና ጉልበት አሳዛኝ ነው:: በሃገሪቱም ሆነ በህዝቧ የወደፊት እጣ ላይ ጨለማ እያጠላ ያለ ጉዳይ ነው::

ከላይ ከተነሱት ጥያቄዎች በተጨማሪ በቅንጀት ማኒፌስቶ ያልተካተቱ ከማኒፌስቶው ዝግጅት በኋላ በተፈጠሩ አዳዲስ ሁኔታዎች አማካይነት በመጡ የድርጅትና የፖለቲካ ጉዳዮች ላይ በስፋት የተሰራ ስራ የለም:: ከእነዚህ ዝግጅት ከሚያስፈልጋቸው ዋኛኛዎቹ ጉዳዮች መሃል አንዱ የድርጅት ገዳይ ነው:: በእኔ እምነት ዛሬ በቅንጅት አመራር መሃል የተነሳውን መለያየት ከየአቅጣቸው በሚሰነዘሩ ተራ ወሬዎችና አሉባልታዎች ብቻ የሚገለጽና እነዚህንም ወሬዎችና አሉባልታዎች በማድርቅ፣ በሽምግልናና በምልጃ የሚፈታ አይደለም:: መሰረታዊ ከሆኑ ድርጅትን በሚመለከት የፍልስፍና የመርህ፣ የህግ፣ የደንብና የስነ ስርአት ጉዳዮች ጋር የተሳሰረ ነው::

አዎን ብዙዎቹ እንደሚሉት ችግሩ በኢኮኖሚ በማህበራዊና በኢኮኖሚ ፖሊሲ ላይ ካለ ልዩነት የመነጨ አይደለም:: ከእዚህ አንጻር ፕሮፌሰር መስፍን እንዳሉት በአመራሩ መሃል የሚታየው ልዩነት የርእዮተ-አለም ወይም የአይዲዎሎጂ ልዩነት አይደለም:: በምርጫው ግዜ ቅንጅት በማኒፌስቶው ባቀረባቸው ፕሮግራሙ ላይና ከወያኔ ጋር በተደገው ክርክር ባስተላለፋቸው መሰረታዊ እምነቶቹ ላይ የሚነሳ ልዩነት እስካሁን አልሰማንም:: *ነገር ግን ቅንጅት በማኒፌስቶው ለህዝብ ቃል የገባቸውን ፖሊሲዎች ለማስፈጸም የሚችልበት፣ አንድ ወጥ ድርጅት ሆኖ ተጠናክሮ የሚወጣበት፣ ድርጅታዊ ፍልስፍናው፣ ቅርጹ ህጉና ደንቡ ወዘተ ምን ይሆናል በሚለው ቁልፍና መሰረታዊ ጉዳይ ላይ በቂ የጋራ ግንዛቤ ያላቸው መሪዎች አባለትና ደጋፊዎች አሉት የሚል እምነት የለኝም::* እነዚህ ጉዳዮች በውህደቱ ወቅት ተነሰተው በተወሰነ ደረጃ መልስ እንደተሰጣቸው ይታወቃል:: በነበረው የወቅቱ ወከባ ይህ ትልቅና እና መሰረታዊ ጉዳይ በቂ ጊዜ፣ ተገቢው ጥናትና ምክክር ተደርጎበት ላለመታለፉ ማስረጃ ፍለጋ እሩቅ መሄድ አያስፈልግም:: ያለንበት ቀውስ ይመሰክረዋል:: ያለጠንካራ ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ደግሞ ቅንጅት ምንም ያህል ውብና የሚያማልሉ ሃገራዊና ህዝባዊ ራእዮች ቢኖሩት ራእየቹ ከባዶ ቃላትነት አልፈው ከቶውኑም በተግባር የሚተረጎሙ አይሆኑም::

ደጋግሜ አጽንኦት ለመስጠት እንደሞከረኩት በውጭም ሆነ በሃገር ውስጥ የተቀሰቀሰው ችግር ሁላችንም ቅንጅት ምን አይነት ድርጅት ነው በሚለው ጥያቄ ላይ አንድ ወጥ የሆነ የጋራ ግንዛቤ ስሌለን የተከሰተ ነው። ይህንን ችግር ሳንፈታ ቅንጅት እንደ ድርጅት ብዙም ፈቀቅ ማለት የሚችል አይመስለኝም።

በተለያዩ ወቅቶች የቅንጅት መሪዎች አሁን በመሃላቸው የተከሰተውን ችግር አቃለው ሲያቀርቡት ይደመጣል። ችግር የለም ይሉናል። ይህ እራሳቸውን መሸንገል ህዝብንም መሸንገል ነው። አባለትና ደጋፊዎች የልዩነቱን ጭብጥ በሚገባ ተረድተው የመፍትሄው አካል እንዳይሆኑ እያደረገ ነው። አየር ማረፊያ በመሄድና ባለመሄድ፣ በየስብሳበው ለመገኘት በመጋበዝና ባለመጋበዝ፣ ከሃገር እንወጣና አንውጣ፣ የላእላይ ምክር ቤት አበላት በስብሰባችን ይሳተፉ አይሳተፉ በሚሉ ችፍቻፊ ጉዳዮች ዙሪያ ያለ ልዩነት በማስመሰል ዋናውን ችግር ወደ ጎን በመግፋት ከችግሩ መውጣት የሚቻል የሚመስላቸው የአመራ አካላት አሉ። ባለፉት ሁለት አመታት ቅንጅት ጠጋ ብሎ በተለይ በድርጅታዊ ጉዳይ ላይ ለማየት እንደእኔ እድል ያጋጠመው ሰው፣ በሃገር ውስጥም ይሁን ከሃገር ውጭ የቅንጅትን ደርጅታዊ ምንነት ለማጤን የቻለ ሰው፣ በተለይ አሁን በቅርቡ በድርጅቱ ውስጥ በአንድ አንድ ወገኖች የተያዘውን ጸረ-ዴሞክራሲያዊ አዝማሚያ በዝርዝር ለሚያውቅ ሰው ችግሩ መሰረታዊ የአመለካከት ልዩነት ችግር ነው።

*«በአንድ በኩል ከሃገርና ከሃገር ውጭ ያለው የቅንጅት እንቅስቃሴ በጎበዝ አለቃና በጭፍሮች የሚመራ ነው የሚል እምነት ያላቸው በእንዲህ አይነቱ እምነት ሁሉንም የቅንጅት እንቅስቃሴ ለመምራት የሚፈልጉ ግለሰቦች ተሰባሰበዋል።»*

*«በሌላ በኩል ቅንጅት ዘመናዊ ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ ነው። የፓርቲው አጠቃላይ ባለቤት አባላቱና ደጋፊዎቹ ናቸው። የሚመራቸውን ይመርጣሉ። የመሪዎቹ ስልጣን የሚመነጨው አባላቱ በምርጫ በሰጧቸው የወክሉኝ መብት ነው። አባላቱ በምርጫ ያወጡትን አመራር በምርጫ ያወርዳሉ» የሚል ነው። «የቅንጅት እንቅስቃሴ ከፍተኛው ስልጣን አባላትና ደጋፊዎች በውክልና ያቆሙት ጠቅላላ ጉባኤ ነው። ቀጥሎም በተዋረድ ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የተቋቋሙ የስልጣን እርከኖች ውስጥ ያሉ ተወካዮች ናቸው» ይላል።*

*«አንደኛው ወገን የድርጅቱ ስራ በጎበዝ አለቃው ፍላጎትና ቀጭን ትእዛዝ መሰራት አለበት ይላል።»*

ሌላው ወገን «የድርጅቱ ስራ ድርጅቱ ባስቀመጠው ደንብና ስርአት የሚገዛ በየእርከኑ ሃላፊነት የተሳጣቸው አካላት መክረውበት፣ በአብላጫ ድምጽ ያለፈው ተፈጻሚ ይሆናል:: በየትኛውም ወቅት በየትኛውም አሰራር ሁሉም የድርጅቱ መሪዎች በአብላጫ ድምጽ የተወሰነን ውሳኔ መፈጸምና ማስፈጸም አለባቸው::» ይላል::

በየመድረኩ የምናየው ድራማ፣ በየሬድዮ ባበያውና በየፓልቶኩ የምንሰማውና በየድረገጹ የምናነበው ከላይ ከገለጽኳቸው መሰረታዊ ቁም ነገሮች ጋር የሚያገኘው ነገር የለም:: የሚነሳው አሉባልታ፣ ተራ ወሬ፣ ስም ማጥፋት፣ ቀረርቶና ፉከራ ዋናውን ጉዳይ እንዳናይ ግልጽ አቋም እንዳንይዝ፣ ፍርዳችንን እንዳንሠጥ ማደናገሪያ አፍዝ አደንግዝ ነው::

በቅንጅት ውስጥ ያለው አደጋ አንዱ አመራር አካል ወይም ቡድን መፍንቅለ-ስልጣን ለማድረግ ከሚያደርገው ጥረት የተነሳ አይደለም:: እየተሞከረ ያለው መፈንቅለ-ስልጣን ሳይሆን መፈንቅለ-ስርአት ለማኪያሄድ ነው:: በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ቅንጅት በሃገር ውስጥና ከሃገር ውጭ የጀመረውንና ገና በመንገዳገድ ላይ ያለውን የድርጅቱን ዴሞክራሲያዊ ስርአት፣ በጎበዝ አለቆቹና በጭፍሮቹ ወደሚመራ፣ የተጠሪነት፣ የተጠያቂነትና የግልጽነት መርህ የተወገዱበት የአሰራር ስርአት የመቀየር ነው:: በሃገር ውስጥ ይህንን መፈንቅለ-ስርአት ከግብ ለማድረስ ሰፊ እንቅስቃሴ ተጀምሯል:: ዝርዝሩ በቅርብ ይወጣል::

በውጭም ድጋፍ ድርጅቶች ዴሞክራሲያዊ መንገድ እንዳይቋቋሙ፣ መሪዎቻቸውን እንዳይመርጡ፣ ከደጋፊዎቻቸው የሚሰበስቡት ገንዘብ የት እንደደረሰ እንዳይጠይቁ፣ የቅንጅትን እንቅስቃሴ ብዙሃንን ያገለለ፣ በጥቂት ምርጦች ምስሌነትና ጭቃሹምነት መመራት አለበት የሚለው ቡድን በቅንጅት ሊቀመንበር ቡራኬ ስራውን እንዲቀጥል ተደርጓል:: እሁድ ኦክተበር 17 2007 ዋሽንግተን ዲ.ሲ ላይ የተደረገው ሁላችንንም በቅንጅት ፓርቲ ዴሞክራሲያዊነትና በሁሉም መሪዎቻችን አርቆ አሳቢነት ስንምል የከረምነውን ሁሉ ያሳፈረና ያዋረደ ስብሰባ ሌላ ትርጉም የለውም::

በቅንጅት የውስጥ ጉዳይ ጣልቃ በመግባት ተራ ወሬ፣ አሉባለታና ሌላም አጸያፊ ፕሮፓጋንዳ የሚያኪያሂዱ ድርጅቶች፣ ወያኔንና ባለፉት 40 ረጅም አመታት የፖለቲካ ህልውናው ውስጥ የዴሞክራሲን ሀ ሁ መረዳት ያቀተውን የተወሰነውን የኢህአፓ አመራር ጨምሮ፣ ይህ በቅንጅት ውስጥ የሚካሄደው ድርጅታዊ ዴሞክራሲን

በሚመለከት የተቀሰቀሰ የውስጥ ትግል በምን መንገዱ ይፈታል የሚለው ጉዳይ ያሳስባቸዋል::

ቅንጅት በኅበዝ አለቃ የሚመራ ድርጅት ሆኖ ከወጣ ምኞታቸው ይሰምርላቸዋል:: ለፈንጠዝያቸው ገደብ አይኖረውም:: አባለቶቻቸው ስለዴሞክራሲዊ ድርጅት በምሳሌነት የሚያቀርቡት የፖለቲካ ሃይል ከመድረኩ ከጠፋ የእነዚህ ድርጅቶች መሪዎቹ አምባገነነናዊ ህይወት ይራዘማል:: የፈጠራ ችሎታቸውን በመጠቀም ብዙ አባላት በባለቤትንት ስሜት የሚሳተፉበትንና የሚቆጣጠሩበትን ዴሞክራሲያዊ የህዝብ እንቅስቃሴ ከመምታት ይልቅ በጎዝ አለቃና በጥቂት ጭፍሮቹ የሚመራን እንቅስቃሴን መምታት ማኮላሸት ቀላል እንደሆነ ስለሚያውቁ በቅንጅት ውስጥ የተጀመረው የውስጠ-ድርጅት ዴሞክራሲያዊ ጥያቄ በኅበዝ አለቃ መመራት በሚፈልገው ወገን አሸናፊነት ቢጠቃለል ደስታቸው ነው::

ዛሬ በአሜሪካ፣ በአውሮፓ፣ በካናዳ፣ በአውስትራሊያ፣ በአፍሪካና በእስያ «ቅንጀት ዴሞክራሲያዊ ድርጅት ነው፤ በሃገራችን ዴሞክራሲ ያሰፍናል» በሚል እምነት በስፋት የተሰባሰበውን፣ የውስጥና የውጭ ፈተናዎቹን ተቋቋቁሞ የሞቱት፣ የተፈናቀሉትና በእስር የሚማቅቁት እንዳይረሱ፣ ባለፉት ሁለት አመታት ከፍተኛውን ትግል ያደረገውን የቅንጅት አካል ማጥፋት የሚቻለው የተጀመረውን ዴሞክራሲያዊ የድጋፍ ድርጅቶች ግንባታ በማኮላሸት እንደሆነ እነዚህ ሃይሎች ያውቃሉ:: የቅንጀት መሪዎች ከእስር ከተፈቱ በኋላም ለወያኔ ሆነ ለየትኛውም የፖለቲካ ድርጅት መሪዎች ተደርጎ የማያውቀውን ደማቅ አቀባባል በአለም ዙሪያ ያስተባበሩት የአካባቢያቸውን ህዝብ አመኔታ ያገኙት እኒሁ ዴሞክራሲን መነሻቸው አድርገው የሚንገዳገዱት የድጋፍ ድርጅቶች ናቸው::

ጸረ ዴሞክራሲ የሆነ አሰራር ያላቸው ድርጅቶች በውጭ የሚኖረው ኢትዮጵያዊ በማምታት ያለምን ተጠያቂነት ገንዘብ ሲያሰባስቡና ሲያባክኑ የነበረበት ሁኔታ የሚያበቃበትን፣ የገንዘብ ምንጫቸው የሚደርቅበትን ሁኔታ መፍጠር የሚችሉት እነዚህ በዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ ተደራጅተው በአለም ላይ ለሚገኘው ሃገር ወዳድ ኢትዮጵያዊ ሁሉ የሂሳብ ደብተራቸውንና እንቅስቃሲያቸውን ግልጽ አድርገው ለማሳየት ቆርጠው የተነሱት ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ የተደራጁት የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶች ናቸው:: ህዝብ ባለፈው ግዜ ለቅንጅት የሰጠው ገንዘብ የት እንደደረሰ በማያውቅበት ሰአት ገንዘብ ሊያዋጣ አይችልም የሚል ፍርሃት በነገሰበት ሁኔታ በየሃገሩ የተሰበሰበው በርካታ ገንዘብ በየአካባበበው ለተቋቋሙት የቅንጅት የድጋፍ ድርጅቶችና ቅንጅትን

*ወክለው በየሃገሩ ለተላኩት መሪዎች ህዝብ ያለውን አመኔታ ያሳያል። ዴሞክራሲን ህዝብን ለመሸንገል ካልሆነ በስተቀር በተግባር ለማዋል ፍላጎቱ በሌላቸው በቅንጅት ውስጥ የሚገኙ ምስለኔዎች እጅ ሆነ በሌሎችም የፖለቲካ ድርጅቶች ቁጥጥር ስር ያሉት ራድዮኖችና ድረገጾች ፓልቶኮች ከወያኔ ጋር የሚደረገውን ትግል በሶስተኛ በአራተኛ ደረጃ አውረደው በሃሰትና በአሉባልታ እሩምታ የቅንጅትን ዴሞክራሲያዊ እንቅስቃሴ ከመስመሩ ለማውጣት የሚያደርጉት ጥረት ሌላ ትርጉም የለውም። ከሰፊው ሃገራዊና ህዝባዊ የወቅቱ አጀንዳ ይበልጥ የግለሰቦችንና የቡድኖችን ጠባብ ጥቅምና ፍላጎት ለማስቀደም ሲባል የሚፈጸም ታሪካዊ ወንጀል ነው። ሃገርና ወገኑን የሚያስቀድም ዜጋ ደግሞ ጉዳዩ ከአሉባልታ ከተራ ወሬና ውሸት ተላቆ በመሰረታዊ ጉዳይ ላይ እንዲያተኩር የማድርግ ግዴታ አለበት። ጉዳዩ ምትሃታዊ አይደለም። ዴሞክራሲያዊ አደረጃጀትና አሰራር ከሞላ ገደል ሁላችንም የምናውቃቸው ስርአቶች ህጎችና ደንቦች አሉት። በቅንጅት ውስጥ የተፈጠረውን ልዩነት በእነዚህ ደንቦችና ህጎች ላይ በመመስረት ጥያቄ በመጠየቅ በቀላሉ ችግር ፈጣሪውን መለየት ይቻላል። በተለይ በአሁኑ ወቅት ላእላይ ምክር ቤቱ ውስጥ ያሉትን አባላት በሙሉ፣ ለእስር የታደረጉትንና ያልተዳረጉትን ጨምሮ ኮረሙ የተሟላ ስብሰባ ይደርግ የሚለው ሃሳብ በሁሉም ተቀባይነት ያለው ስለሚመስል ማንኛውንም ጉዳይ ወደ ምክር ቤቱ ወስዶ ምክርቤቱ በሚሰጠው ውሳኔ መገዛት ብቻ ነው። ጥያቄው ምክርቤቱ ተሰብስቦ የሚያሳልፈውን ውሳኔ ለመቀበል ሁሉም ፈቃደኛ ነውን ነው? ለእዘህ መልሱ አዎን ከሆነ ጊዚያዊ ችግራችን ያበቃለታል። በበኩሌ ግን እስካሁን ከሚታየው አዝማሚያ ከተፈጸመው ድርጊት በሃገር ቤትና ከሀገር ውጭ እየተደረገ ያለው ዝግጅት ሁሉም ፋቃደኛ አይመስለኝም። በሃገር ቤትና በውጭ ሃገር ቅንጅትን የሚደግፈው ሃይል ግን ከዴሞክራሲያዊ አሰራር ውጭ የሚሄድን የትኛ ውንም ቡድን የማይደግፍ መሆኑን በግልጽና በማያሻማ ቋንቋ አስቀምጦ በሁሉም ላይ ተጽእኖ በማሳደር ካለንበት ችግር ልንወጣ እንችላለን። ይህ ግን ከጊዚያዊ እፎይታ በላይ የሚዘልቅ አይሆንም። በመሃከለኛና በረጅሙ ዘመን ሊነሱ ስለሚችሉት ድርጅታዊ ችግሮቻችን ግን ካሁኑ መዘጋጀት ይኖርብናል። ከእዚህ ቀጥሉ እንድታነቡ የምጋብዛችሁ ጽሁፎች ዘለቄታነት ባላቸው ድርጅታዊ ችግሮችና በመፍትሄያቸው ዙሪያ የተጻፈ ነው። በቀጥታም ይሁን በተዛዋዋሪ ካሁኑ ችግሮቻችንም ጋር በብዙ ክሮች የተሳሰረ ጽሁፍ ስለሆነ በጥሞና አንብቡት እላለሁ።*

ከእዚህ በታች የሚቀርበው ጽሁፍ በምርጫ 97 ማግስት የተጻፈ ነው። ምርጫው እንዳለቀ በእዛው የግንቦት ወር ቅንጀት ወደ ውህደት ማምራቱ የማይቀር መሆኑን፣ ይህ ውህደት ግን ፈተናና ችግር የበዛው ይሆናል በሚል ስጋት ድርጅቱን ለመርዳት ሲባል ከአንድ የቅርብ ጓደኛዬ ጋር በመተጋገዝ ያዘጋጀነው ነበር። መንደርደሪያ አድርጌ

ያቀረብኩት ጽሁፍ ደግሞ ዋናው ጽሁፍ ከተጻፈ በኋላ በእዚህ ጽሁፍ ላይ ህብረተሰባችን ውይይት እንዲጀምር ለማድረግ በአንድ ወቅት በቅንጅት ጽፈት ቤት አማካይነት መታተም ተጀምሮ ለነበረው «የቅንጀት ድምጽ» ተብሎ ይጠራ ለነበረው ጋዜጣ የጻፍኩት ነው።

ሁለቱም ጽሁፎች አሁን ቅንጅት ላላበት ችግሮቹን የሚጠቁሙ የወደፊቱንም አደጋ የሚያሳዩ መፍትሄውንም የሚያመላክቱ ነጥቦች ያዘሉ ናቸው የሚል እምነት አለኝ። ለእዚህም ነው ቀደም ብለው ያነበቡትም ሆነ አዲሶቹ አንባቢዎች በቅንጅት ውስጥ ባለፉት ሁለት አመቶች የታዘቡትን እንዲመረምሩበት እንደገና ለንባብ ያቀረብኩት። ሁለቱም ጽሁፎች በጥናት ላይ የተመሰረቱ በመሆናቸው ችግሮችን አስቀድመው በማየትና መፍትሄ በማስቀመጥ የጥናትና የምርምርን አስፈላጊነት በማጠናከር ጥሩ ምሳሌዎች ይሆናሉ እላለሁ። ጽሁፍ ቢበዛ፣ ቲዎሪ ቢበዛ፣ ፍልስፍና ቢበዛ ምን ያደርጋል የሚሉ አሉ። በሃገራችን ከፍተኛ የቲዎሪ፣ የጽሁፍና የፍለስፍና ድህነት እንጂ ተቃራኒው ታይቶ አይታወቅም። ትልቁ ችግራችን ሳናስብና ሳናቅድ መስራት መሆኑን መረዳት ይኖርብናል።  ምሁራዊ ስንፍና ወይም የአቅም ማጣት ካልሆነ በስተቀር ጥናትና ምርምር ቅንጅትን ለመሰለ ዘመናዊ የፖለቲካ ፓርቲ ወሳኝነት ያለው ጉዳይ እንጂ ምሁራዊ መቀናጣት እንዳልሆነ በተለይ በድርጅቱ አመራር ላይ የሚገኙ ግለሰበች ሊገነዘቡት ይገባል።

በእዚህ ጽሁፍ የቀረቡትን ሃሳቦች መንደርደሪያ በማድረግ በራሳችን መሃል ወይይትና ክርክር በማድረግ በድርጅት ጉዳይ ግልጽነት ያለው የጠራ አቋም እንዲኖረን ማድረግ እንችላለን። መሪዎቻችንም ተጨባጭ በሆኑ ሃሳቦች ዙሪያ ለመሞገት ያስችለናል ብዬ አምናለሁ። ይህን ጸሁፍ በወቅቱ ሰጽፈው በሃገራችንና ከሃገራችን ውጭ ቅንጀትን የሚደግፈው ኢትዮጵያዊ የቅንጅትን ውህደት የተሳካ ለማድረግ ተጽአኖ ማድረግ የሚችልበትን አቅም ለማስታጠቅ እንዲቻል በድረገጾች ለማሰራጨትና አሳትሞ በስፋት በሃገር ውስጥ ለመበትን ነበር። ማሳተሙ ባይቻልም ይህ ጽሁፍ በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ከውህደቱ በፊት በድረ-ገጽ ወጥቶ ነበር። በቅንጀትም ውስጥ መወያያ ሆኖ ነበር።

ቅንጅት ወደ ውህደት ሲሸጋገር ውህደቱን ለማስፈጸም ችኮላ ላይ ስለነበር የውህደቱን ጉዳይ ቴክኒካዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት ሙከራ አደረገ እንጂ ለህዝብ የገባውን የዴሞክራሲ ቃል ኪዳን እውን ለማድረግ ድርጅቱ ምን አይነት ድርጅታዊ ፍለስፍና ያስፈልገዋል የሚለው ጉዳይ በአመራሩ ውስጥም ሆነ በሰፊው አባላቱና የድርጅቱ ደገፊዎች ዘንድ ውይይትና ክርክር ሳይደረግበት ቀረ። በተለይ ከኋላ ቀር ባህላችን አንጻር

ሊመጡ የሚችሉ ችግሮች እየተነሱና እየተተቹ በአደረጃጀት ጉዳይ ላይ የአመለካከትና የአስተሳሰብ ለውጥ ሳይደረግ ውህደቱን ቴክኒካዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት የተደረገው ሙከራ ዛሬ በድርጅቱ ውስጥ የምናየውን ውዝግብና ውዥንብር አስከተለ:: ዛሬም ቢሆን ከእዚህ ችግር መውጣት የሚቻለው ሁሉም በጋራ የተስማማበትንና ያመነበትን አንድ ወጥ የአደረጃጀት ሃሳብ ሲጋራና ይህንንም በተግባር ለመፈጸም ቆርጦ ሲነሳ ነው:: ይህንን ግምት ውስጥ ያላስገባ እርቅ፣ ስምምነትና አንድነት ወደፊት አመርቅዞ ለሚነሳ ሌላ መናቆር በር ከፋች እንጂ የችግራችን የዘለቄታ ፈውስ ሊሆን አይቸልም::

አዎን ጽሁፉ ረጅም ነው:: በአንድና በሁለት ገጾች በየድረገጹ የሚወጡ ስሜታዊ ጽሁፎችን ማንበብ ለለመደ የድረ ገጽ አንባቢ እንደሚያስቸግር አውቃለሁ:: ረጃጅም ጽሁፎች ለማንበብ ብዙ ሰው ትእግስት እንደሌለውም አውቃለሁ:: ረጃጅም ጽሁፎች ማንበብ የማይፈልጉ ግለሰቦች ቀጥሎ  መንደርደሪያ በሚል ርእስ የሰፈሩትን ጥቂት ገጾች ማንበብ ይችላሉ:: ዛሬ በቅንጅት ውስጥ የምናየው ትርምስ በእነዚህ ጥቂት ገጾች አስቀድሞ የታየ መፍትሄውም በእነዚሁ ገጾች የተጠቆመ መሆኑንም መገንዘብ ይችላሉ:: ለቅንጅት ችግር ፈረንጆቹ እንደሚሉት ፈጣን መድሃኒት (quick fix) የለውም :: ግዜን የሚበላ፣ እውቀትን፣ ብልሃተኛነትና ትእግስተኛነት የሚጠይቅ ነው:: በመጨረሻም ፍላጎቱና አቅሙ ያለው ይህንን ጽሁፍ በድምጽም ይሁን በሌላ መንገድ አባዝቶ ማሰራጨት ይችላል::

<u>**መንደርደሪያ**</u>

<u>**ቅንጅት እና የውህደት ጥያቄ**</u>                    **አንዳርጋቸው ጽጌ  ግንቦት  1997**

የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ድርጅት እና ስልጣን (Political Parties: Organisation and Power) በሚለው መፅሐፉ አንጀሎ ፓኔብላንኮ (ANGELO PANEBIANCO) የተባለ የፖለቲካ ፓርቲዎች ጉዳይ ተመራማሪ ሊቅ የተናገረውን በመጥቀስ እጀምራለሁ:-

«በተለያዩ ዙሮች ካርታው ከታደለ በኋላ በአንድ ድርጅት የጨቅላነት እድሜ የተገኙ የአደረጃጀት ውጤቶች፣ የዚህን ድርጅት የወደፊት እጣ በበርካታ መንገዶች በመወሰን ለአስርተ አመታት የሚዘልቅ ተጽዕኖ ይኖራቸዋል::»

ይህንን አባባል አንጀሎ የሰነዘረው በአለማችን ያሉትን በርካታ እና ታላላቅ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ታሪክ ካጠና በኋላ ነው:: የፖለቲካ ድርጅቶች ሲመሰረቱ አደረጃጀትን በሚመለከት የሚተክሏቸው ፖሊሲዎች፣ ያሚያቆሟቸው ድርጅታዊ መዋቅሮች፣ የሚደነግጓቸው ድርጅታዊ ሕገ ደንቦች እና የሚወስዷቸው አቋሞች በቀላሉ ሊቀየሩ የማይችሉ መሆናቸውን የብዙ ፓርቲዎችን ታሪክ በማጥናት አንጀሎ የደረሰበት መደምደሚያ ነው::

የፖለቲካ ድርጅቶች ታሪክ በሙሉ፣ ከወግ አጥባቂ ድርጅቶች አንስቶ እስከ ተራማጅ ነን የሚሉትን ድርጅቶች ጨምሮ፣ ታሪካቸው የሚያሳየው ተመሳሳይነት ያለው ድርጅታዊ ለውጥን እና ማሻሻያ ያለመቀበል ባህርይ ያላቸው መሆኑን ነው::

የፖለቲካ ድርጅቶች አንዴ ከተቋቋሙ በኋላ እራሳቸውን እንደነበሩ የማስቀጠል ከፍተኛ የወግ አጥባቂነት ባህርያት አላቸው:: ለእዚህ ነው ቅንጅትን የመሰለ ድርጅት ከጥምረት ወደ ውህደት በሚያደርገው ጥረት አንጀሎን ከመሳሰሉ የፓለቲካ ፓርቲዎች ሊቃውንት አስተያቶች ትምህርት ለመቅሰም ዝግጁ መሆን ያለበት::

ቅንጅት በጨቅላነቱ የሚቆምባቸው የድርጅት ፍልስፍና እና የሚከተላቸው የድርጅት ፖሊሲዎች፣ ለዘመናት የድርጅቱን የፖለቲካ ምንነት እና ማንነት የሚወስኑት ይሆናሉ:: እስከ አለንበት ወቅት በሀገራችን የፖለቲካ ታሪክ ከታዩት ፓርቲዎች ጋር ሲነጻጸር ቅንጅት ተወዳዳሪ የማይገኝለት ዴሞክራሲያዊ ፓርቲ የመሆን እና ያለመሆን እጣው የሚወሰነው በእዚህ የውህደት የጨቅላነት እድሜው በሚጥላቸው መሰረቶች ላይ ብቻ ነው::

ቅንጅት ሁላችንም የምንመኘው ዴሞክራሲ ድርጅት እንዲሆን ለማድረግ በአመራሩ እና በአባላቱ ውስጥ በበርካታ ድርጅታዊ ጉዳዮች ላይ ጥልቀት ያላቸው ውይይቶች መደረግ ይኖርባቸዋል:: በእነዚህ ጉዳዮች ላይም በከፍተኛ ደረጃ መግባባት ያስፈልጋል:: የቅንጅት ድምፅም፣ የቅንጅት አመራሮችን አባላትን እና ደጋፊዎችን የተለያዩ አመለካከቶች በማስተናገድ ወደፊት ለሚደረገው ድርጅታዊ ውህደት ትልቅ ድጋፍ መስጠት ይጠበቅበታል:: በእነዚህ ፅሁፍ የማነሳው ወደፊት ሊነሱ ከሚገባቸው ጥያቄዎች መሃል አንዱን ነው:: ይህም የታሰበው ውህደት በምን መልኩ የሚለውን ይሆናል?

በተለያዩ ሃገሮች ከሚገኙ የብዙ ዘመን እድሜ ካላቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች ሆኑ በሃገራችን ወሳጥ ባለፉት ጥቂት አስርተ አመታት ከተፈጠሩ ፓርቲዎች ታሪክ

የምንማረው አንድ ቁም ነገር አለ፡፡ ይህም የፖለቲካ ፓርቲዎች አመሰራረት በዋንኛነት በሁለት አይነት መሠረታዊ ሂደቶች የሚከናወን መሆኑን ነው፡፡

የመጀመሪያው፣ ተመሳሳይነት ያለው የፖለቲካ እምነት እና አመለካከት ያላቸው ጥቂት ግለሰቦች በጋራ በመሰባሰብ የሚጀምሩት ፓርቲ ይሆናል፡፡ የእዚህ አደረጃጀት የተለየ ባህርይ ከመጀመሪያው ጀምሮ በግለሰብ ደረጃ የሚመለመሉ አባላትን የድርጅቱ መሰረት እና የእድገቱ ምንጭ አድርጎ የሚቀጥል መሆኑ ነው፡፡ በአባላት ላይ አባላትን እየጨመረ በሂደት በመቶ ሺዎች እና በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ አባላት የሚኖሩት የብዙሃን ፓርቲ አደረጃጀት ነው፡፡ እንዲህ አይነቱ አደረጃጀት የዴመክራሲ እምነት ባላቸው ግለሰቦች እስከተመራ ድረስ የአባላቱን የእኩልነት እና ዴሞክራሲያዊ መብቶች እንዲከበሩ በማድረግ ከጅማሮው ድርጅታዊ መረጋጋት የሚኖረው ይሆናል፡፡

በእንዲህ አይነቱ ድርጅት ውስጥ የአመለካከት ልዩነቶች ቢነሱም ሰላማዊ እና ዴሞክራሲያዊ በሆነ መንገድ፣ የድርጅቱን ሕልውና ሳያናጉ የሚፈቱበትን ሁኔታ ለማመቻቸት የተሻለ ዕድል ያለው ይሆናል፡፡ ብዙዎቹ በአለም ላይ እረጅም እድሜ ያላቸው ባለብዙ አባለት ዴሞክራሲያዊ የፖለቲካ ፓርቲዎች በእንዲህ አይነት መንገድ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ ሌላው እና ሁለተኛው የአደረጃጀት አይነት የተለያዩ የፖለቲካ እና ፖለቲካዊ ያልሆኑ ድርጅቶች በቅድሚያ በጥምረት ወይም በግንባርነት ቀጥሎም ወደ ውህደት የሚሄዱበት አደረጃጀት ነው፡፡

እንዲህ አይነቱ አደረጃጀት ከመጀመሪያው አይነት አደረጃጀት ጋር የሚመሳሰልበት ነጥብ አለው፡፡ በግንባሩ ወይም በጥምረቱ የሚገቡት ተናጠል ድርጅቶች በጥቂት ግለሰቦች ተመስርተው አባላትን እያበዙ የሚሄዱ መሆናቸው ነው፡፡ ሆኖም ግን በተለያዩ ምክንያቶች፣ ከአቅም ማነስ ወይም ብቻቸውን በጀመሩት መንገድ ለመቀጠል እንዳይችሉ የሚያደርጉ ከበባዊ ሁኔታዎች ሲያጋጥማቸው ተመሳሳይነት እና ተቀራራቢነት ካላቸው ድርጅቶች ጋር በቅድሚያ በመተባበር በግንባር ወይም በጥምረት ብሎም ወደ ውህደት ያመራሉ፡፡ ይህ ውህደት ሁለት አይነት አቅጣጫዎች ሊከተል ይችላል፡፡

አንደኛው እና በሰፊው የተለመደው ድርጅቶቹ በሰው ሀይል፣ በቁሳቁስ፣ በገንዘብ እና በሌሎች መመዘኛዎች በተስማሙባቸው መስፈርቶች መሰረት የየድርጅቶቹን ስልጣን፣ የሐላፊነት ድርሻ አስቀድሞ በድርድር በመስማት በየድርጅቱ አመራሮች መሃል የሚደረግ ውህደት ነው፡፡ የአንዱን ድርጅት መሪ ሊቀመንበር፣ የሌላውን ምክትል ሊቀመንበር ወዘተ በማድረግ በሚፈጠረው ምክር ቤት እና ስራ አስፈጻሚ ኮሚቴ

ከየድርጅቱ የሚወከሉ አባላትን ቁጥር ወዘተ የመሳሰሉት አስቀድሞ በመስማማት የሚፈጠር ውህደት ነው፡፡ በእንዲህ አይነቱ መንገድ ወደ ውህደት የሚመጡ የፖለቲካ ፓርቲዎች ብቻ ሳይሆኑ የፖለቲካ ፓርቲዎችን ለመፍጠር ወይም ለመደገፍ ፈቃደኛ የሆኑ ጠንካራ የሙያ ማህበራትና ሌሎች ማህበራዊ ድርጅቶች በመተባበር የሚመሰርቱት ሊሆን ይችላል፡፡ ከፖለቲካ ድርጅቶች ጋር ድርድር በማድረግ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ የሰራተኛ እና የመምህራን ማህበራት ከመሳሰሉት ጋር በመተባበር እንዲህ አይነቱ ፓርቲ ማቆም ይችላሉ፡፡ ልክ እንደ ፓርቲዎች ውህደት፣ የሙያ ማህበራቱ እና መሰል ማህበራዊ ድርጅቶች፣ በተዋሃደው ፓርቲ የተለያዩ የስልጣን እርከኖች ውስጥ የሚኖራቸውን የመቀመጫ ብዛት ወይም ድምፅ በቅድሚያ በመስማማት ከፖለቲካ ፓርቲዎች ጋር በመጣመር ፓርቲዎችን የመሰረቱባቸው ሁኔታዎች በበርካታ የአውሮፓ አገሮች ውስጥ ተከስቷል፡፡ ብዙዎቹ የአውሮፓ የሶሻል ዴሞክራቲክ ፓርቲዎች ይህን በመሰለ መንገድ የተመሰረቱ ናቸው፡፡ የእንግሊዝ የሌበር ፓርቲ ለእዚህ አይነቱ አደረጃጀት ቀዳሚ ምሳሌ ነው፡፡

እንዲህ አይነቱ አደረጃጀት ፌዴራላዊ በሆነ መንገድ የእያንዳንዱን ድርጅት ህልውና አስጠብቆ የሚቀጥል ነው፡፡ ድርጅቶቹ እና አባላቱ የድርጅቶቻቸውን አመለካከት እና እምነት በድርጀቱ ወስጥ ለመከላከል ሁሌም በተጠንቀቅ የቆሙ፣ የተዋሃደው ድርጅት የሚወስናቸውን ውሳኔዎች በቅድሚ ከድርጅቶቻቸው ጥቅም አኳያ እያሰሉ የሚቃወሙበት ወይም የሚደግፉበት ሁኔታ ባህላቸው ሆኖ የሚታይበት ነው፡፡

ይህ አደረጃጀት በመጀመሪያው ወቅት ድርጅቶችን በማቀራረብ እና ወደ ህብረት እና ውህደት እንዲመጡ ለማድረግ የሚያመች ቢሆንም ውሎ-አድሮ ስር በሰደደ ድርጅታዊ ህልውና እና ጥቅም ባላቸው ድርጅቶች ፍላጎቶች ፓርቲውን በመናቆር እንዲኖር ያደርገዋል፡፡ ትንሹንቃሮ ትልቁንም ውሳኔ ላይ ለመወሰን ማለቂያ የሌላቸው የየድርጅቶቹን የተናጠል ውሳኔ የሚጠብቅ ጎታችና ቅልጥፍና የሌለው አሰራር የሚያስከትል ነው፡፡ውሳኔዎች ሕዝብን እና ሃገርን ይጠቅማል ወይ ከሚሉ መስፈርቶች ይበልጥ ድርጅታችንን ይጠቅማል ወይስ ይጎዳል ወይ በሚሉ መስፈርቶች እየተለኩ ቅዋሜ ወይም ድጋፍ የሚያገኙበትን ሁኔታ የሚያመቻች ይሆናል፡፡

*<u>በትንሹም በትልቁም ልዩነት ድርጅታዊ መሳሳብ ስለሚፈጠር ከውህደቱ እወጣለሁ፤ አባላቴን እና ንብረቴን ይዤ እሄዳለሁ፤ በሚል ማስፈራሪያ ሁሌም የፓርቲውን ህልውና ማናጋት፣ ፓርቲውን በጥቅሉ የሚደግፈውን ህዝብ ጭንቀት ውስጥ የሚጥሉ ሆኔታዎች በተደጋጋሚ እንዲከሰቱ የማድረግ አደጋዎች በተደጋጋሚ የሚከሰቱበት ይሆናል፡፡</u>*

*በተለይ የዴሞክራሲያዊ ባህል ባልዳረባቸው ሃገሮች ውስጥ፣ በድርጅቶች መካከል የሚነሱ ልዩነቶች ለመፍታት ሰፊው የፓርቲ አባላት በበቂ መረጃ ተደግፈው ግራና ቀኘ-ን አይተው መወሰን የሚችሉበት ሁኔታ አይኖርም:: በመሆኑም የየድርጅቱ መሪዎች አባሎቻቸውን በቀላሉ የፍላጎቶቻቸው ማስፈጸሚያ ለማድረግ የሚቸግራቸው አይሆንም:: አባላቱን የትክክለኛ መረጃ ባለቤቶች እንዳይሆኑ፣ በቂ የመወያያ ጊዜ እና ነጻነት እንዳይኖራቸው በማደረግ የራሳቸወን የአባላቱን ብቻ ሳይሆን ሕብረተሰባቸውን ጥቅም የሚጥሱ  ውሳኔዎችን እንዲወስኑ ማድረግ ቀላል ነው::*

*በእዚህ መንገድ ወደ ህብረት የመጡ ድርጅቶች አንዱ ሌላውን እየጠበቀ ስለሚኖር ስፋት ያለው ውስጠ-ድርጅት ዴሞክራሲ አይኖረውም:: በሃገራችንም ሆነ በሌሎች ሃገሮች እንደታየው በእንዲህ አይነቱ ፓርቲ ውስጥ አንዱ ሌላውን ለማጥፋት በሴራ በተንኮል ግዜን ማባከን የተለመደ ነው:: ውሎ አድሮም በሂደት ደካሞቹ የፓርቲ ድርጅቶች በትልልቅና በጉልበተኞቹ ፓርቲዎች የሚደመሰሱና የሚዋጡ፣ አልያም በስም ብቻ ነፃ ድርጅቶች ሆነው የሚቀሩበት ሁኔታ ይፈጠራል:: በሃገራችን በደርግም ሆነ በወያኔ/ኢህአዴግ ዘመን በእዚህ አይነቱ የውህደት መንገድ የተፈጠሩ ድርጅቶች ውለው አድረው በጥምረት ከገቡት ድርጅቶች መሃል የአንደኛው ድርጅት እና ብሎም የአንድ ግለሰብ ትእዛዝ አስፈጻሚ ሆነው የቀሩበት ምክንያት ከላይ ከጠቀስነው ችግር ጋር የተያያዘ ነው::*

ሌላው የውህደት መንገድ የሁሉንም አባል ድርጅቶች አባላት በአንድ ውህድ ድርጅት አባልነት በማዛወር የሚፈጸመው ነው:: በእንዲህ አይነቱ ሁኔታ ከላይ በአመራር አካላት አማካይነት የሚደረግ ውህደት አለመሆኑ ጠባብ የድርጅት ፍላጎቶች ተጠናክረው የማይቀጥሉበት፣ በጠባብ የቡድን ስሜት አባለት እየተከፋፈሉ የማይናቆሩበት፣ አባለት የሁላችንም ድርጅት ነው ብለው ለሚያምኑበት ፓርቲ መጠናከር በጋራ የሚሰሩበትን ሁኔታ በቀላሉ መፍጠር ይቻላል:: የድርጅቶቹ አመራሮችም እንደማንኛውም ተራ የድርጅቱ አባላት ተቆጥረው በውህደቱ ስለሚቀላቀሉ የየራሳቸውን የቀድሞ ስልጣን በርስተ-ጉልተነት ይዘው ወደ ተወሃደው ፓርቲ አይመጡም:: የተዋሃደው ፓርቲ አባላት ገና ከመጀመሪያው  በብቃትና በችሎታ መስፈርቶች፣ አዳዲስ መሪዎቻቸውን «በአንድ ሰው አንድ ድምፅ» መርህ አማካይነት ስለሚመርጡ ድርጅቱን ገና በጨቅላ እድሜው ዴሞክራሲያዊ፣ አመራሩንም ብቃት ያለው ለማድረግ የተመቻቸ ሁኔታ ይፈጥራል:: የድርጅታቸውን መሪዎች በጋራ የመረጡ አባላትም ስልጣን የሰጧቸውን መሪዎቻቸውን

